# ❖አራተኛ ዙር የጥያቄዎች መልስ❖



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ

ጳጉሜን ፭፤ ፳፻፲፫ ዓ.ም

## ❖አራተኛ ዙር የጥያቄዎች መልስ❖

፩. በቅዱስ ሩፋኤል በዓል (በጳጉሜን 3) የሞተ ሰው ስለኃጢአቱ አይጠየቅም፣ ዝም ብሎ ወደ ገነት ይገባል የሚሉ ሰዎች አሉና እንዴት ነው እውነታው?

> መልስ፦ ቅድስት ቤተክርስቲያን እንዲህ ያለ አስተምህሮ የላትም:: ማንኛውም ሰው በሠራው ኃጢአት ይጠየቃል:: ጳጉሜን 3 ስንሞት በኃጢአት የማንጠየቅ ከሆነማ ሁላችንም በዚህ ቀን እንሙት እንዴ? እንዲህ ያለ የቤተክርስቲያን ትምህርት ያልሆነን ነገር የቤተክርስቲያን አስመስለው የሚናገሩ ሰዎችን ልንታገሣቸው አይገባም:: ማስጠንቀቅና ካልተመለሱም አውግዞ መለየት ያስፈልጋል:: ወደ ገነት ለመግባት ማመን፣ መልካም ሥራን መሥራት፣ ምሥጢራትን መፈጸም ነው::

፪. አንድ ሰው በሥጋ ድንግል ነበር:: ምንም ዓይነት ግንኙነት አድርጎ አያውቅም:: ነገር ግን በሁለት አጋጣሚ ከበፊት ፍቅረኛው ጋር ተሳስሚል ተሽክሚታል:: እና በሆነ ስብከት ላይ አንድ አባት "ተሳስሞ ተክሊል አይቻልም" ሲሉ ሰምቶ (ኃጢአት መሆኑ እንዳለ ሆኖ) ከዚህ በኃላ what is the point of keeping my Virginity? መሳሳም ብቻ ካስቀረ ሲል ይሄ ነገር የሰባኪው የግል አመለካከት እንጂ ፍትሐ ነገሥቱ የሥጋን ድንግልና ብቻ ጠቅሶ ሌላውን ለንስሐ አባት Judgment ትቶታል ብሎ አንዱ ሐሳብ አነሳ:: በዚህ ጉዳይ የቤተክርስቲያን መልስ ምንድን ነው?

> መልስ፦ ሳያገቡና ሳይጋቡ በፍትወታዊ ስሜት ሆኖ መሳሳም ኃጢአት ነው:: ይህ ቁጥሩ ከመዳራት ነውና (ገላ.5፥19):: ይሁንና ድንግልናን ያሳጣል የሚለውም አርቆ ለማጠር ሲባል የተነገረ ካልሆነ በስተቀር ልክ አይደለም:: ስለዚህ ንስሓ ገብተው ዲያቆናትም በአገልግሎት ይቀጥላሉ:: ያላገቡም ንስሓ ገብተው በተክሊል ይጋባሉ::

፫. ሰዓታት ለኖኅ ሐመሩ ላይ "ጊዜ ትወፅእ ነፍስከ መንጦላዕተ ምኵራብ ተሠጠ፣ ፀሐይ ደንገፀ ወወርኀ አንሶጠጠ፣ ትስብእትከ ጊዜ ተፈልጠ" ይላል:: ትስብእትከ ጊዜ ተፈልጠ ሲል ምን ለማለት ነው?

> መልስ፦ "ትስብእትከ ጊዜ ተፈልጠ" ሰውነትህ በተለያየ ጊዜ ማለት ነፍስና ሥጋህ በተለያየ ጊዜ ማለት ነው:: ሰው ሰው የሚባለው ነፍስና ሥጋ ሲዋሐዱ ነውና:: ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ በመስቀል በተሰቀለ ጊዜ ቅድስት ነፍሱን ከክብርት ሥጋው በራሱ ሥልጣን ለይቷልና ይህንን ለመግለጽ ትስብእትከ ጊዜ ተፈልጠ ብሏል እንጂ መለኮትስ ከተዋሕዶ በኋላ ለቅጽበት ያህልም አልተለየም::

፬. ሁሉም ሰዎች በሃይማኖታቸው መሠረት ትክክል ከሠሩ በየሃይማኖታቸው ይጸድቃሉ የሚሉ አሉና ምን እንበላቸው?

መልስ፡- ይህ አባባል ትልቅ ስሕተት ነው፡፡ ሃይማኖት አንዲት ናት (ኤፌ.4፥5)፡፡ ከአንዲቷ ሃይማኖት ውጪ ያለ ሰው አይድንም፡፡ እንኳን የሌላ እምነት ሰው ሊድን ከአማኞችም ምግባር የሌለው ሰው አይጸድቅም፡፡ ሃይማኖት ያለ ምግባር፣ ምግባር ያለ ሃይማኖት አያድንም (ያዕ.2፥17)፡፡

## ፳. እግዚአብሔር መሓሪ ርኅሩኅ ቸር ደግ ቅን የዋህ ነው ሲባል ምን ማለት ነው? ለ30 ዓመት ሙሉ ካደረብኝ ደዌ ፈውሰኝ ብየ ብለምነው እምቢ አለኝ፡፡ ይኼ ከቸርነቱ ከይቅር ባይነቱ ጋር ይስማማል ወይ? በዚህ ደዌ ምክንያት የሚደርሱብኝ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ልቤን ሲያደክሙት እያየ ዝም ማለቱ ከመሓሪነቱ ከይቅር ባይነቱ ጋር ይስማማል ወይ?

መልስ፡- የእግዚአብሔር መሓሪነት ከሰው ልጆች እሳቤ በላይ ነው፡፡ ደዌን በተመለከተ አራት አይታዎች አሉ፡፡ አንደኛውና ሁለተኛው ደዌ ዘመቅሰፍትና ደዌ ዘኃጢአት የሚባሉት ናቸው፡፡ እነዚህ በበደል ምክንያት የሚመጡብን በሽታዎች ናቸው፡፡ እነዚህም ለእኛ ተግሣጽ ይሆኑን ዘንድ የሚመጡብን በሽታዎች ናቸው፡፡ ሁለተኛውና ሦስተኛው ደግሞ ደዌ ዘዕሴትና ደዌ ዘንጽሕ ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ የሰው ልጅ በዚህ ምድር መከራ በበዛበት መጠን በዘለዓለማዊ ሕይወቱ ዋጋው ይበዛለታልና ሰማያዊ ዋጋችን ይበዛ ዘንድ ከሰዎች የተለየ ኃጢአትን ሳንሠራ በዚህ ዓለም በሽታና ሌሎችም መከራዎች ይደርሱብናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ በሽተኛዎች እንደነበሩ ተገልጿል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲያውም በሽታውን እንዲያርቅለት እግዚአብሔርን ለምኖት ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን ልመናውን አልተቀበለውም (2ኛ ቆሮ.12፥7-9)፡፡ ስለዚህ ታግሠን እግዚአብሔርን እያመሰገንን ብንኖር ሰማያዊ ዋጋ እናገኝበታለንና እንታገሥ፡፡ መታከም የሚችል ከሆነ ደግሞ በሕክምናም በጸበልም መሞከር ነው፡፡

## ፳፩. ጊዜ መች ተፈጠረ? ለምን ከሥነ ፍጥረት ጋር አንቆጥረውም?

መልስ፡- ጊዜ በድርጊቶች መካከል ያለውን የድርጊት ቅደም ተከተል የሚያሳውቀን ህልውናው በድርጊቶች ላይ የተመሠረተ ጥገኛ ሀላዊ ነው እንጂ ራሱን ችሎ አካል ያለው ፍጥረት አይደለም፡፡ ለምሳሌ ሦስት ሰዎች በአንድ ላይ ሲኖሩ "አንድነት" አላቸው ይባላሉ፡፡ ይህ አንድነት በሰዎች ላይ የተመሠረተ የሰዎችን በአንድ ላይ መኖር መግለጫ እንጂ ራሱን ችሎ አካልና ህልውና ያለው ነገር አይደለም፡፡ ጊዜም እንዲሁ ነው፡፡

## ፳፪. የዲያቆናት ቀድሶ ማግባት በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እንዴት ይታያል?

መልስ፡- በዚህ ዙሪያ የሚከለክልም፣ የሚፈቅድም ሥርዓት አላገኘሁም፡፡ ከሥርዓቱ አንጻር ስናየው ሥርዓተ ተክሊሉ ሲፈጸም አንድ መነናጸፊያ ይለብሳሉ ተብሏል፡፡ ይህ

ግን በተክሊል ሥርዓቱ ጊዜ የሚደረግ ነው:: ከዚያ በኋላ በቅዳሴው ስላለው ጉዳይ ምን መሆን እንዳለበት የሚገልጽ አላገኘሁም::

፰. በቊርባን የተጋቡ ባልና ሚስት ከልጅ መምጣት በኋላ ቢጣሉ ባይስማሙ እና ሴቷ ላይ በጣም ከባድ የሆነ የሕይወት ጥያቄ ቢፈጥርባት ማለትም በሕይወቷ ላይ እንዲሁም በአእምሮዋ ወይም በሥነ ልቦና ከባድ የሆነ ጫና ቢደርስባት መፍታት ኃጢአት ይሆንባታል? እስከ ምን ድረስ ነው እየተሰቃየች እንድትኖር የሚፈረድባት? እግዚአብሔር የሴትን ልጅ ስቃይ ይወዳል? ምንም ቢፈጠር አብራ ትኑር ካልኖረች ግን እፈርድባታለው ብሏል?

መልስ፦ ጋብቻ ክቡር ነው:: በጋብቻ ደግሞ መፈተን አለ:: ፈተና የሌለበት ጋብቻ የለም:: ፈተናን ታግሦ መኖር ጽድቅ ይሆናል:: ምንም ክቡር ቢሆን ፍቺ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎችም ግን አሉ:: እነዚህም ከሁለት አንዱ ከሌላ ዘንድ ሲያመነዝር ቢገኝ፣ ሃይማኖት ቢቀይር፣ አንዱ አንዱን ለመግደል እስኪደርስ ድረስ ጥላቻ ካደረበት፣ ለሩካቤ የማይመች ተፈጥሯዊ ነገር በሴቷ ወይም በወንዱ ካለ [ለምሳሌ የወንዱ አባለ ዘሩ የሽንብራ አፍንጫ የምታህል ሆና ለሽንት ብቻ ከሆነችና ፍትወትን ማራቅ የማይችል ከሆነ ለሦስት ዓመት ታግሠው ይፋታሉ:: የሴቷ አፈ ማሕፀንም ለግንኙነት የማይመች አጥንትና መሳይ ነገሮች ካለባት]፣ ፍናፍንት ከሆነ፣ አንዱ ቢሞት፣ በፈቃድ ቢመነኩሱና በመሳሰለው ከተገኙ ፍቺ ይፈቀዳል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24):: ሌሎች ጉዳዮችም ካሉ ጉዳዩን ለንስሓ አባት ገልጾ ችግር ያለበትን ሰው እንዲገሥጸው ማድረግና አብሮ መቀጠል ነው:: እግዚአብሔር ለሴትም ለወንድም እኩል እይታ አለው:: የአንዱን መበደል አይፈቅድም::

፱. በዚህ ዓመት ወንድ ልጄን ክርስትና ለማስነሳት ወደ አንድ ደብር አቀናሁ:: ከዚህ ቀደም በነበርኩበት ሌላ ክልል አንድ ልጄን ክርስትና ሳስነሳ ቤተ ክርስቲያኗ ራሷ በአንገት የሚታሰር ማዕተብ በክርስትና ቤት ውስጥ አዘጋጅታ አስቀምጣለች:: ከዚያም ለሕፃኑ ይታሰርለታል:: አሁን በሥራ ቅያሬ ምክንያት ወደ አማራ ክልል ተቀይሬ ከመጣሁ በኋላ ሌላ ሁለተኛ ልጄን ክርስትና ለማስነሣት ወደ አንድ ታላቅና ስመጥር ደብር አመራን:: ዘመነ ፋሲካ ስለሆነም ሌሊት 10:30 ሄድን:: ማታ ከ3:00 በኋላ ከጎረቤቶቻችን ጋር ስናወራ ለሕፃኑ የሚታሰር ማዕተብ ያዙ አሉን:: ቤት ውስጥ ፈላልገን ነጭ፣ ጥቁር እና ሰማያዊ ቀለም ያለው ማዕተብ በርከት አድርገን ያዝን:: ሌሊት 11:30 ላይ መጽሐፈ ክርስትናው መደገም ሲጀመር ማዕተብ አምጡ ተባልን:: ሁሉም ሰው የያዘውን ቀይ፣ ጥቁርና ነጭ ሆኖ የተገመደ ማዕተብ ሲያቀርብ እኔ የያዝኩትን ጥቁር፣ ነጭና ሰማያዊ ያልተገመደ ማዕተብ አሳየሁ:: ካህኑ ይሄ አይሆንም:: ቀይ፣ ጥቁርና ነጭ አይደለም አሉኝ:: ለዚያውስ ይሄንን ሁሉ ያመጣኸው ጥጃ ልታስርበት ነው እንዴ አሉኝ:: እውነቱን ለመናገር ከአንድ የሃይማኖት አባት ይኼን በመስማቴ ውስጤ ቅር ቢለውም አሁን የተባለውን ማተብ ከየት ማግኘት እችላለሁ አልኳቸው:: ውጣና ከሱቅ ግዛ አሉኝ:: ስወጣ

ሌሊት ስለሆነ ሱቆቹ አልተከፈቱም። ተመለስኩና አላገኘሁም አልኳቸው። እኔ አይመለከተኝም የኔ ሥራ መጽሐፈ ክርስትና መድገም ነው አሉኝ። በዚህ መካከል በየግድግዳው ማፈላለግ ጀመርን። ከሌላ ልጆች የተረፈ ይመስለኛል የሚፈለገው ዓይነት ማተብ አገኘንና ሥርዓቱም ተፈጸመልን። ከዚህ ሰዓት ጀምሮ በውስጤ የሚያጭሩ ጥያቄዎች አሉ። እኔን ጨምሮ በገጠሪቱ ቤተክርስቲያን የተጠመቅን ሰዎች በሥርዓተ ጥምቀታችን ጊዜ የታሰረልን ማግ (ከጥጥ ብቻ የተዘጋጀ ፈትል) ነበር። ስለዚህ ከሥርዓት ውጭ ነን ማለት ነው? እንደተባለው ዓይነት ማተብ ባይገኝስ ሥርዓተ ጥምቀቱ አይፈጸምም ማለት ነው?

መልስ፦ አማረልን ብለን የምንናገረው ንግግር ምን ያህል በሌሎች ላይ ተጽእኖ እንዳለው ከዚህ ጽሑፍ መረዳት ይቻላል። ስንነጋገር ቀልድም ቢሆን ሌሎች ላይ የሚፈጥረውን ክፉ ስሜት አስቀድመን ተረድተን ማስቀረት አለብን። የቄሱ አነጋገር መታረም አለበት። ወደ ፍሬ ሐሳቡ ስንመጣ ማተብ ማድረግ የተጀመረው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በያዕቆብ ዘእልበረዲ [ዘአልቦ ረዳኢ] አማካኝነት ነው። ይኸውም አማኙን ከኢአማኙ ለመለየት ያደረገው ነው። ስለዚህ በልጅነታችን ምንም ዓይነት ማተብ ቢደረግልን የክርስትናችን ማረጋገጫ ጥምቀቱና ሥጋውን ደሙን መቀበላችን ስለሆነ ከሥርዓት ውጪ ነን አያሰኘንም። ማተብ ስለጠፋ ተብሎ ደግሞ ሥርዓተ ጥምቀቱ ይቋረጥ አይባልም። ከተጠመቀ በኋላ ይደረግለታል። የማተብ ዓይነቱ በቀኖና የተደነገገ አይደለም። ነጭ ብቻ የሚያደርግ አለ፣ ጥቁር ብቻ የሚያደርግ አለ፣ ነጭ ጥቁርና ቀይ በአንድ ላይ ገምደው የሚያደርጉም አሉ። ምስጢሩ መለያ ምልክት ስለሆነ በየትኛውም ቢሆን የሚያመጣው ችግር የለም።

## ፲. የንስሓ አባት መቀየር ይቻላል ወይስ አይቻልም?

መልስ፦ የንስሓ አባቱ ችግር ያለበት ከሆነ መቀየር ይቻላል። በዘመናችን ቅድስት ቤተክርስቲያንን ከሚያሰድቡ ሰዎች መካከል ክፉ የሆኑ አንዳንድ ንስሓ አባቶች አሉ። ገንዘብ የሚጠይቁና ልጆችን የሚያሳቅቁ፣ ኃጢአታቸውን ከተናዘዙ በኋላ ለሌላ ሰው የሚናገሩ፣ ይህንን ካላደረጋችሁ ኃጢአታችሁን ነው ለሰው የምናገር እያሉ የሚያስፈራሩ አሉ። እንዲህ ያሉትን ፈጥኖ መቀየር ይገባል። ስንቀይራቸው ግን ተሰናብተናቸው ልንሄድ ይገባናል። አላሰናብትም ብሎ ድርቅ ካለ ለሰበካ ጉባኤ አሳውቆ ወደ ሌላ መሄድ ነው። [የተናዘዛችሁትን በደል እናገራለሁ እያለ ለማሳቀቅ የሚሞክርና የማትፈልጉትን እንድታደርጉ የሚያሳቅቃችሁ ቄስ ካለ በአደባባይ እንድናሰጣው ንገሩን]።

## ፲፩. ጥንተ ቀመር ከሠሉስ የተጀመረበት ምክንያት ምንድን ነው?

መልስ፦ ቀመረ-ቆጠረ ከሚለው ግሥ ቀመር ይወጣል። ቁጥር ማለት ነው። ዘመናትን ወደኋላ ስንቆጥር ወር አንድ ብሎ መቆጠር የተጀመረ ማክሰኞ ስለሆነ ማክሰኞ ጥንተ

ቀመር ይባላል። ዓለም የተፈጠረ መጋቢት 29 እሑድ ነው። መጋቢት 30 ሰኞ ይሆናል። እነዚህ ዕለተ ጠቢባን ይባላሉ። ማክሰኞ ሚያዝያ 1 ይሆናልና በዚህ ምክንያት ነው። ቁጥር አንድ ብሎ የተጀመረበት በመሆኑ ማክሰኞ ጥንተ ቀመር ይባላል።

**፲፪. የክርስቶስ ልደትን ለመጠበቅ በፀሐይ፣ በጨረቃ፣ በከዋክብት ይቆጥሩ ነበር የሚል አለ። በከዋክብት እንዴት ነው የሚቆጠረው?**

መልስ፦ ሕልመልመሌክ፣ ብርክኤል፣ ናርኤል፣ ምልክኤል የሚባሉ አራቱን ወቅቶች ማለትም ጸደይን፣ ክረምትን፣ መጸውን፣ በጋን የሚመግቡ ከዋክብት አሉ። እነዚህ ከዋክብት 91 ቀን ከ15 ኬክሮስ ይመግባሉ። ስለዚህ እነዚህን ከዋክብት መሠረት እያደረጉ የጌታን መምጣት በሱባኤ ይቆጥሩ ነበር ማለት ነው።

**፲፫. በአንዳንድ አካባቢ ጳጉሜን 3 በሩፋኤል ቀን 365 አቡነ ዘበሰማያት ድገሙ እና ኃጢአታችሁ ይሠረያል ይባላል እና ልክ ነው?**

መልስ፦ ጸሎት ለሰው ልጅ አስፈላጊ ነገር ነው። በጸሎትም ሥርየተ ኃጢአት፣ በረከት፣ ረድኤት፣ ፈውስና የመሳሰሉ ጸጋዎች ይገኛሉ። ስለዚህ 365 ጊዜ መጸለይ ጥቅሙ ትልቅ ነው። 365 ቀን ጸልዩ የሚል ሥርዓት ግን የለም። መምህራን ባለፉ 365 ቀናት የሠራነውን ከንቱ ሥራ አስበን እንድንፀፀት በማሰብ በግላዊ አስተያየት 365 ጸልዩ ሊሉ ይችላሉ። ይህ ግን እንደ ግላዊ በጎ አስተያየት ልናየው እንችላለን እንጂ የሕብረታዊቷ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ነው ብለን አንናገርም። ሌላው የምናስታውሰው ኃጢአት ካለ ንስሓ መግባት ነው። ጸሎት ኃጢአትን ያስተሠርያል ብለን የምናስታውሰውን ኃጢአት ለንስሓ አባት ከመናገር ወደኋላ ማለት አይገባም።

**፲፬. የቅዳሴ መጽሐፍ ለምንድን ነው ከቁርባን በኋላ አትታጠቡ የሚለው? ውሃ መንካት፣ መተጣጠብ ለምን ይከለከላል?**

መልስ፦ የቆረበ ሰው መንግሥተ ሰማያት የገባ ሰው ምሳሌ ነው። መንግሥተ ሰማያት ከገባን በኋላ የሚኖረን ሰውነት ደግሞ የከበረ ሥጋ በመሆኑ መታጠብን አይሻም። በዚያ ምሳሌ ስንቆርብ ሰውነታችን የከበረ መሆኑን እንድንገነዘብ አባቶች እንዳንታጠብ ሥርዓት ሠርተውልናል።

**፲፭. ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ስንሄድ ፊታችንን ውሃ ማስነካት እንደሌለብን ተነግሮናል። ለምንድን ነው?**

መልስ፦ በአፋችን፣ በአፍንጫችን ውሃ እንዳይገባብን ነው:: ጾመን መቊረብ ይገባናልና:: ሰውነታችን ደግሞ የከበረ ሥጋውንና ደሙን ሊቀበል በመሆኑ ከእርሱ በፊት መግባት ያለበት ሌላ ምግብና መጠጥ መኖር ስለሌለበት ነው::

፲፮. ድጓ፣ ቅኔ፣ መጽሐፍ፣ አቋቋም፣ ቅዳሴ፣ ዝማሬ…ወዘተ ተምሮ የሀብታም ዘበኛ፣ የባጃጅ ሹፌር፣ ሱቅ በደረቴ ሠሪ መሆን ይቻላል ወይስ አይቻልም?

መልስ፦ መንፈሳዊ መምህርም ቢሆን ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች መሥራት በደል አይሆንበትም:: ይችላል:: ክህነቱን የሚያዋርዱ ሥራዎችን መሥራት ነው የማይገባው እንጂ ማንኛውንም ሥራ ሠርቶ መለወጥ ይችላል:: ነገር ግን ቤተክርስቲያን የአገልጋይ እጥረት ካለባት መደበኛውን የቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዲያገለግሉ በቤተክርስቲያን መመደብ ይገባል::

፲፯. በብዙ ቤተክርስቲያናት ላይ የበረከት ሥራ በማለት በግዝት በዓላት ቀን ሥራ ይሠራል:: በዓልን መሻር አይሆንም?

መልስ፦ ይሆናል:: ምንም እንኳ የምንሠራው ሥራ ለቤተክርስቲያን ቢሆንም በግዝት በተከለከሉ በዓላት ድካም ያለበት ሥራን መሥራት አይገባም:: በዓላት ከዳግም ትንሣኤ በኋላ በመንግሥተ ሰማያት ለምንኖረው ሕይወት ምሳሌዎች ናቸው:: በመንግሥተ ሰማያት ደግሞ ፍጹም ዕረፍት እንጂ ድካም የለም:: በመሆኑም በበዓላት አድካሚ ሥራን መሥራት ስለማይገባ ለቤተክርስቲያንም ቢሆን ማረስ፣ መቆፈር፣ ሕንፃ መሥራትና የመሳሰሉ ሥራዎችን መሥራት አይገባም::

፲፰. ክፉን መሥራት እንጂ መብላት ኃጢአት የለውም (አለመጾም ኃጢአትነት የለውም) የሚሉ ብዙዎች አጋጥመውኛልና ምን ልበላቸው?

መልስ፦ ስለጾም አስፈላጊነት ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አስተምሮናል:: ስትጾሙ እንደ ግብዞች አትሁኑ የሚለው ቃሉ ጾምን የሚያረጋግጥና ሂደቱ ምን መሆን እንዳለበት የሚያሳይ ነው (ማቴ.6፥16፤ ማቴ.17፥21):: በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጾሞ አሳይቶናል (ማቴ.4፥2):: ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንም ይህንን መሠረት አድርገው በፍትሐ ነገሥት ቀኖና ሠርተዋል [አንቀጽ 15]:: ሳይታመም የማይጾም ካህን ቢኖር ከክህነቱ እንደሚሻርና የማይጾም ምእመንም መኖር እንደሌለበት ተገልጿል:: ስለዚህ በቀኖና አለመሥራት ራሱ ኃጢአት ስለሆነ አለመጾም ኃጢአት ነው::

፲፱. ሌሊት ስናወጣ የየወራቱን ሕፀፅ እንደምራለን:: ነገር ግን ከጥቅምት ወደ ኅዳር፣ ከታኅሣሥ ወደ ጥር፣ ከየካቲት ወደ መጋቢት፣ ከሚያዝያ ወደ ግንቦት እና ከሰኔ ወደ ሐምሌ ስንሻገር ሕፀፁ ስለሚቀያየር ሌሊቱ በሁለት ቀን ይጨምራል:: ሕፀፁ ሲቀየር ነው ሌሊቱ

በሁለት የሚቀየረው። ለምሳሌ የጥቅምት 30 ሌሊቱ 24 ቢሆን በነጋታው የኅዳር 1 ሌሊቱ 26 ያድራል። ስለዚህ እንዴት ሌሊቱ 24 ብሎ 25ን ዘሎ ቅደም ተከተል ሳይጠብቅ 26 ሆነ?

መልስ፦ ሕፀፅ የሚነግረን ጨረቃ የምትጠፋበትን ጊዜ ነው። ጨረቃ በሁለት ወር አንድ ጊዜ ትጠፋለች። ስለዚህ የጨረቃን ጠፍነት ለመግለጽ በየሁለት ወሩ አንድ አንድ ቀን ይዘላል። በሌሊት ታበራ ዘንድ ሌሊትን የምትመግብ ጨረቃ ጠፍ ስለምትሆን በየሁለት ወሩ ሌሊቱ አንድ ቀን ይዘላል (ዘፍ.1፥16)።

፳. የሰው ልጅ በየቀኑ በኀልዮ፣ በነቢብ፣ በገቢር ኃጢአትን ሊሠራ ይችላል። ለኀልዮውም በየቀኑ ንስሓ መግባት አለብን ወይስ በየቀኑ ከካህን መስቀል ስንሳለም ይሠረያል የሚባለው እውነት ነው?

መልስ፦ መስቀል ስንሳለም የሚሠረየውን ኃጢአት እኛ አናውቀውም። እግዚአብሔር ባወቀ ይቅር የሚለውን ይቅር ይላል። እኛ ግን ወደ ንስሓ አባታችን ስንቀርብ ያስታወስነውን በደል ሁሉ መናዘዝ ይገባል። የኀልዮውንም፣ የነቢቡንም፣ የገቢሩንም እንናዘዛለን። ከዚህ ሁሉ ንጹሕ እስክንሆን ድረስ መመላለስ ይገባል።

፳፩. አንድ ክርስቲያን የንስሓ አባቱን ልጅ ማግባት ይችላል?

መልስ፦ አዎ ይችላል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ላይ የተከለከሉ ጋብቻዎች አራት ዓይነት ናቸው። እነዚህም የሥጋ ዝምድና፣ የክርስትና እናት አባት ዝምድና፣ የጋብቻ ዝምድና፣ የማደጎ ዝምድና ናቸው። የንስሓ አባትና የቀለም አባት ልጅን ማግባት ከእነዚህ ውስጥ አልተካተተም። ስለሆነም ማግባት መጋባት ይቻላል።

፳፪. እውነተኛው ሃይማኖት ምንድን ነው? በምን ማረጋገጥ ይቻላል?

መልስ፦ እውነተኛዋ ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ናት። ይኸውም ከአዳም ጀምሮ ስትያያዝ የመጣች፣ ለነቢያት በተለያየ መንገድ የተገለጸች፣ በኋላ በራሱ በክርስቶስ ሰው መሆን የተረጋገጠች፣ በሐዋርያት የተሰበከች፣ በሐዋርያት ተከታዮች ሊቃውንት የተመሰከረች ያልተቋረጠች ከእግዚአብሔር የተገለጠች እምነት ናት። ማረጋገጥ የሚቻለው በመገለጥ፣ በታሪክ፣ ጥንታዊ ሰነዶችን በመፈተሽ፣ በቅብብሎሽ፣ በእምነት፣ በጸሎትና በመሳሰሉት ማረጋገጥ ይቻላል። የሁሉንም እምነት መነሻ በመመርመር አእምሮን በመጠቀምም በጥቂቱ ማመዛዘን ይቻላል።

፳፫. በትዳር ሰዓት መጠናናት ያስፈልጋል ይባላል። እና ግን ምኑን ነው የምንጠናነው? ለምሳሌ እንደ ጣይብ ፋቂ፣ ቡ*ዳ፣ ባርያ እያሉ ወዘተ በጣም ችግር አለ። እነዚህን ነገሮች እንዴት ይታያሉ?

መልስ፦ የሚጠናው ሃይማኖቷ/ቱ ምን እንደሆነ፣ ዝምድና እንዳይኖር ዝምድናን ለመቁጠር ነው። በተጨማሪም ለመጠናናት እንዲያመች የራሱ የሆነ የእጮኝነት ጊዜ አለ [ፍት.ነገ.24]። በዚህ ጊዜ የምንጠናናው ጸባይን፣ አመለካከትንና የመሳሰሉትን ነው። ሃይማኖታቸው ክርስቲያን ከሆኑ ሽማኔ፣ ፋቂ፣ ቡ*ዳ፣ ባሪያ፣ ጣይብ፣ እጀ ሠሪ...ወዘተ የሚባሉ ነገሮች መስፈርት አይሆኑም። በጥምቀት ክርስቲያን ከሆንን በኋላ በሁላችንም መለያየት የለምና። መጋባት ይቻላል። "አልቦ በዝንቱ አይሁዳዊ፣ ወአልቦ አረማዊ፣ አልቦ ነባሪ፣ ወአልቦ አግዓዚ፣ አልቦ ተባዕት ወአልቦ አንስት፣ ዳእሙ ኵልክሙ አሐዱ በኢየሱስ ክርስቶስ" እንዲል (ገላ.3፥28)። እነዚህ ነገሮችም የምእመናንን አንድነት ለመከፋፈል የባዕድ [የውጭ] ሰዎች ያመጧቸው ማለያያ ግድግዳዎች ስለሆኑ መቀበል የለብንም።

፳፬. በእግዚአብሔር ዘንድ ትናንትና የለም ነገም የሚባል የለም በእርሱ ዘንድ ሁሌ ዛሬ ነው የምንል ከሆነ ትናንትና እና ነገ የሌለው ዛሬ ምን ዓይነት ዛሬ ነው?

መልስ፦ እግዚአብሔር ከጊዜና ከቦታ ውጭ ነው። ራሱ በራሱ ይኖራል። ለእርሱ ጊዜውም ቦታውም ራሱ ነው። ይህንን የሚያውቀው ደግሞ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ እኛ ልናብራራውም ልንናገረውም አንችልም። እኛ ፍጡራን መናገር የምንችለው ፍጡር ስለሆኑ ቦታዎችና ስለፍጡራን ጊዜ ብቻ ነውና። እግዚአብሔር ትላትና ዛሬ ያው ነው። በትላንቱና በዛሬው መካከል መለወጥ የለበትም (ሚል.3፥6)። መለወጥ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ጊዜን ማሰብ ራሱ ከፍጥረት ኀሊና በላይ ነው።

፳፭. በጸሎተ ፍትሐት ጊዜ የሚታረደውን በግ በቤት ውስጥ ማረድ ይፈቀዳል ወይ?

መልስ፦ ከቅጽረ ቤተክርስቲያን ውጪ ይሁን እንጂ የትም መታረድ ይችላል። ቤተክርስቲያን ውስጥ ማረድ ግን አይቻልም። ቤተክርስቲያን የሚፈተትና የሚሠዋ የክርስቶስ ሥጋና ደም ብቻ ነውና። በፍትሐት ጊዜ የሚበላ፣ የሚጠጣ ይዘን መሄዳችንም ካህናቱ ለዚህ ብለው ሥራ ፈትተው ስላገለገሉ ዋጋቸው ስለሆነ ነው። "...ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና" እንዲል ጌታ (ማቴ.10፥10)።

፳፮. ዲያቆን እርድ ማረድ ይችላል ወይስ አይችልም?

መልስ፦ ይችላል። እንዳያርዱ የሚታዘዙት ቀሳውስት ናቸው እንጂ ዲያቆናት አይደሉም። ቀሳውስት እንዳያርዱ ሥርዓት የተሠራውም የክርስቶስን ሥጋና ደም በቆረሱበትና ባፈሰሱበት እጃቸው የፍጡርን ደም ማፍሰስ ስለማይገባቸው ነው። ዲያቆናት ግን ሥራቸው ተልእኮ ብቻ ስለሆነ ማረድ ይችላሉ።

፳፤. ጳጉሜን 6 የሞተ ሰው የዓመት ፍትሐቱ መቼ ነው የሚደረገው? ጳጉሜን 6 የተወለደ ሰውስ ዓመቱ የሚሞላ መቼ ነው?

መልስ፦ ይህ ጥያቄ የጳጉሜን 6 አመጣጥን ካለመረዳት የመጣ ሐሳብ ነው። በየዓመቱ ያለው 15 ኬክሮስ በአራት ዓመት 60 ኬክሮስ ሞልቶ የፈጠረው ነው። በየዓመቱ በጳጉሜን 5 እና በመስከረም 1 መካከል 15/15 ኬክሮስ አለ። የዚያ ድምር በአራት ዓመት አንድ ቀን ሞላ ይባላል። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ቢወለድም ቢሞትም በ365 ቀን ከ6፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ስለሆነ በዚህ ጊዜ መሠረትነት ተጠንቶ ፍትሐቱ ይከናወናል። በዘመነ ሉቃስና በዘመነ ዮሐንስ ጳጉሜን 6 ትሆናለች። ይህ ማለት መስከረም 1 ቀን ጠዋት ይገባል ማለት ነው። የሥነ ፍጥረት ዕለታት ከምሽት እስከ ምሽት ይቆጠራሉ። ጳጉሜን 6 ሆነ የምንለው የየዓመቱ 6፡00 ሰዓት በአራት ዓመት 24፡00 ሰዓት ሆኖ ነው። ያ ማለት የአራተኛዋ ዓመት ስድስት ሰዓት ከባለፉት ትርፎች ቀጥላ ከሌሊቱ 6፡00 ሰዓት እስከ ጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ባለው የሆነች ናት። ይህ ደግሞ በሥነ ፍጥረት አቆጣጠር ወደ ቀጣዩ ቀን ስለሚከበር በሦስቱ ዓመት መስከረም 1 ይሆናል ማለት ነው። ፍትሐቱም ልደቱም ይህንን መሠረት አድርጎ ይሄዳል። በራሷ ጊዜ ደግሞ በዚያው በጳጉሜን 6 ይደረጋል።

፳፭. አንድ ሰው አጥብቆ የሚፈልገው ነገር እንዲፈጸምለት ሱባኤ ይይዛል። ከሱባኤው በኋላ የጠየቀው ጥያቄ ባይመለስለት ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር አልደረሰም ማለት ነው? የዚያስ ሰው እምነት አይሸረሸርምን?

መልስ፦ የሰው ልጅ የሚፈልገውን ነገር ለመጠየቅ ሱባኤ ይገባል። ሱባኤ መጠየቂያ ነው። ምላሽ መስጠት አለመስጠት የእግዚአብሔር ድርሻ ነው። ሰው ተስፋ አድርጎ ይጸልያል። እግዚአብሔር ደግሞ ለሚገባው የሚገባውን ይሰጠዋል። ሱባኤ ስለገባበት ተብሎ የተጠየቀ ሁሉ አይሰጥም። ለጠያቂው የሚጠቅመው ከሆነ ይሰጠዋል። ለጠያቂው የማይጠቅመው ከሆነ አይሰጠውም። ስለዚህ ሱባኤ የሚገባ ሰው መጀመሪያ የእግዚአብሔርን አሠራር ማወቅ አለበት። ሱባኤ የተገባበት ነገር ሁሉ አይሰጥም። የሰው ድርሻ መጠየቅ ብቻ ነው። የጠየቀው ነገር ስላልተፈጸመለት እምነቱ ከተሸረሸረ ይህ ሰው መጀመሪያም ስለክርስትና በቂ ግንዛቤ ስለሌለው ሊያስተምሩት ሊማር ይገባል። የለመነው ካልተሰጠው ባይጠቅመኝ ይሆናል ብሎ አመስግኖ መኖር ነው። የለመነው ቢሰጠውም ማመስገን ነው።

፳፮. በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 1 ላይ “ምእመናን ያልሆኑ ሰዎች ወይም ሥጋውንና ደሙን ከመቀበል የተወገዙ ምእመናን ወደ እርሷ እንዳይገቡ የቤተ ክርስቲያንን በሮች ይጠብቋቸው” ይላል። ሆኖም በጉብኝት ሰበብ እምነታቸው ሌላ እንደሆነ የሚታወቁና የማይታወቁ ሰዎችን

(በተለይ የውጭ ሀገር ሰዎችን) ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማስገባት እናስጎበኛለን። ይህ ከሥርዐት አንጻር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ አይቻልም። ይህ ሁኔታ የተፈጠረው በብዙ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። በዋናነት ግን ሁለት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። አንደኛው የካህናት አጎብዳጅነት ፈሪነት የፈጠረው ነው። ሁለተኛው ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ካለማወቅ የተፈጠረ ነው። የፈረንጆቹ ችግር አይታየኝም። ምክንያቱም ይህ ቤተክርስቲያን ነው የእምነቱ ሰዎች ሥርዓት ደግሞ አማኝ ያልሆነ ስለማይገባ አትገቡም ቢባሉ አይቀየሙም። ይህ በሌሎች ዓለሞችም ጎብኚዎች ከሩቅ ብቻ የሚያዩዋቸው የማይገቡባቸው ቦታዎች ይኖራሉ። ስለዚህ ይህ የእኛ ችግር ነው። ማስተካከል አለብን። የሌላ እምነት ሰው ወደ ቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ መግባት የለበትም።

፴. ሥልጣነ ክህነት የሌለው ሰው ንዋየ ቅድሳትን ተባርከውና ከብረው ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት ካልሆነ ለአገልግሎት ከዋሉ በኋላ መንካት እንደማይቻል የመጽሐፈ ቅዳሴው አንድምታ ያዝዛል (ምዕራፍ 1 ቍ.26)። በከተሞች ሴቶች ልብሰ ተክህኖ እንዲያጥቡ ይደረጋል። ይህ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ይህም ባለማወቅ የሚደረግ ስሕተት ነው። ክህነት ያለው ሰው ብቻ የሚለብሳቸው አልባሰ ክህነት አሉ። እነዚህን ሌላ ሰው እንዳይነካቸው በፍትሐ ነገሥትም ተገልጿል። ስለዚህ መታጠብ አለባቸው ተብሎ ከታሰበ እንኳ በካህናት ብቻ ይታጠባሉ እንጂ ክህነት በሌላቸው በሰንበት ተማሪዎች፣ በምእመናን...ወዘተ ሊነኩ አይገባም።

፴፩. መጽሐፈ ቅዳሴ አንድምታ ገጽ 149 ቍ.45 ላይ "ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ቢነጥብ ምን ይሁን? ቢሉ ከማየ መቍረር አስቀድሞ ቢሆን አንሥተው ቀዳስያኑ ይላኩታል። ከማየ መቍረር በኋላ ማለት ጠበል ከጠጡ በኋላ ቢገኝ ግን በጽዋው አድርገው በማጎፈድ ሸፍነው አሳድረው በነጋው መሥዋዕት ሠርተው እንደገና ቀድሰው በደም ጠምተው ይቀበሉታል" ይላል። መሥዋዕቱን ለነገ አታሳድሩ ከሚለው ጋር አይጋጭም?

መልስ፦ መሥዋዕትን ለነገ ማሳደር አይገባም። ከቀዘቀዘ የክርስቶስ ሥጋ መለኮት ያልተዋሐደው ዕሩቅ ብእሲ ነው የሚል ምሳሌያዊ ትርጉምን ያመጣልና ነው። ስለዚህ መሥዋዕትን በዕለቱ ተዘጋጅቶ በዕለቱ ይላኩታል እንጂ አያሳድሩትም። ከማየ መቍረር በኋላ ሥጋውን ደሙን መቀበልም አይቻልም። ማየ መቍረር በፊት ሆኖ ሥጋውና ደሙ ከተከተለ ማየ መቍረር ከቍርባን ይበልጣል ያሰኛልና ነው። ስለዚህ የተሻለው መፍትሔ የነጠበውን አሳድሮ ከአዲሱ ጋር ጠምቶ መልላክ ነው። አታሳድሩ የተባለው ከድንገት የነጠበውን ሳይሆን ሙሉውን ነውና።

፴፪. በፊደል ገበታ ላይ ከሌሎቹ መልእክታት እና መጻሕፍት ተለይቶ መልእክተ ዮሐንስ ለምን ተደረገ?

መልስ፦ የዮሐንስ ወንጌል ዝሙት ለሚያስቸግረው በቀን ሦስት ምዕራፍ በሳምንት 21ዱንም ምዕራፍ ቢያነበው ቢጸልየው ያስታግሠዋል ብለው አባቶች በትርጓሜ ገልጸዋል:: ስለዚህ እንደሌሎች የጸሎት መጻሕፍት ለብቻውም እየታተመ ይገኛል:: የፊደል አዘጋጁም የንባብ መለማመጃ ይሆን ዘንድ የዮሐንስ ወንጌልን አብሮ አሳትሞታል:: የሌሎችም ተጨምሮ መደረግ ይችላል:: ፍሬ ነገሩ የንባብ መለማመጃ እንዲሆን ታስቦ ነው::

፴፫. አሁን አሁን ዲያብሎስን የሚያስንቅ ኃጢአት እያየን እየሰማን ነው:: እና የእኔ ጥያቄ አንቀጸ ንስሓ ላይ ካለው በላይ ለሚፈጸም ኃጢአት መፍትሔው ቀኖናው እንዴት ነው?

መልስ፦ ቀኖናን በተመለከተ ከተጻፉ የቀኖና መጻሕፍት ውጭ የሆነ የማይታወቅ በደል ካጋጠመ ንስሓ አባት ሁኔታውን ገምግሞ ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ ምጽዋትና የመሳሰሉትን ይወስንለታል:: ከባድ ነው ተብሎ የታሰበና በብዙዎች ዘንድ የሚስተዋል ከሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ አዲስ የቀኖና መጽሐፍ ማዘጋጀት ይችላል::

፴፬. አንድ ዲያቆን ወይንም ቄስ ክህነቱን በአንድም በሌላም ነገር ካፈረሰ በኋላ ዲያቆኑ በዲቁና ስም ይጠራል ወይስ አይጠራም?

መልስ፦ አይጠራም:: ዲያቆንም ቄስም ክህነታቸውን ካፈረሱ በኋላ እንደሌላው ምእመን "አቶ" ተብለው ይጠራሉ እንጂ በቀድሞ የክህነት ስማቸው ዲያቆን ወይም ቄስ ተብለው አይጠሩም::

፴፭. በክርስትና እምነት ባል እና ሚስት ወሊድ መከላከያ መጠቀም ይችላሉ? ካልቻሉስ ምንድነው መፍትሔው ማለት ለልጅ የሚሆን በቂ ሀብት ባይኖራቸው እና የአንዱ ፈቃድ ቢያስቸግርስ?

መልስ፦ የወሊድ መከላከያ መጠቀም አይቻልም:: ከጋብቻ መሠረታዊ ዓላማዎች አንዱና ዋናው ዘር ለመተካት ነው:: ስለዚህ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች እንጂ ሸክሞች ስላልሆኑ ላለመውለድ የወሊድ መከላከያን መጠቀም አይገባም:: ከዚያስ ወልደን ለማሳደግ የሚሆን በቂ ገንዘብ የለንም ካልን በቂ ገንዘብ እንዲኖረን ምን እናድርግ ምን እንሥራ የሚለው ላይ በጥልቀት ብናስብበት መልካም ነው::

፴፮. በጉባኤ ቤት ውስጥ በጾም ወቅት ሥጋ የነካው ኮቸሮ መመገብ የተለመደ ነው:: ይህ እንዴት ይታያል?

መልስ፡- ከጾም ሕጎች አንዱ የፍስክ ምግቦችን አለመመገብ ነው፡፡ የፍስክ ምግብ የሚባለው ደግሞ የእንስሳት ተዋጽኦ የሆኑ ሥጋን፣ ወተትን፣ እንቁላልን፣ ቅቤንና የመሳሰሉትን ነው፡፡ እነዚህ የነካኩት ምግብ የፍስክ ምግብ ስለሆነ በጾም ወቅት መብላት አይገባም፡፡ እኛ በችግር የምንኖር ነን እያልን ለራሳችን አስተያየት እየሰጠን መብላት የለብንም፡፡ ስለዚህ በጾም ወቅት የጾም ኮቸሮ መብላት ነው የሚገባው፡፡

፴፯. የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ተነቅለህ ሂድ ብትሉት ይሆንላችኋል ከሚለው አንጻር ዛሬ ይህ ሁሉ ሊቃውንት እና ምእመናን ምን ደረጃ ላይ ነው ያለው?

መልስ፡- ይህንን መጀመሪያ መሠረታዊ ሐሳቡን መረዳት ይገባናል፡፡ የሰናፍጭ ቅንጣት ማለት ምን ማለት ነው? የሰናፍጭ ቅንጣት ምንም ነቅዕ የሌለባት ናት፡፡ ስለዚህ ምንም ነቅዕ የሌለበት መታመን ያለው ሰው ተራራውን ተነቅለህ ሂድ ቢለው ይሄዳል ማለት ነው፡፡ ይህ መታመን ደግሞ የሰው ልጅ በቅድስና ልምምድ ሲበቃ የሚያደርገው እንጂ ብዙ ሰው ስለተሰበሰበ የሚያደርገው አይደለም፡፡ ስለዚህ ተራራ ለማፍለስ የሚያበቃ ምግባር እንዲኖረን ሁላችንም መጣር አለብን፡፡ ተራራ ከማፍለስ ይልቅ ግን ሥነ ምግባር ያለን ሰዎች መሆን ይበልጣል፡፡ በተአምራት ሙት ከሚያስነሣ ሰው ንስሓ የሚገባ ሰው ይበልጣል፡፡ ተአምር ማድረግን ኃጥኣንም ያደርጉታልና፡፡

፴፰. ትክክለኛውና እውነተኛው አምላክ ማን ነው? ይህ አምላክ መሓሪና ይቅር ባይ እንደሆነ በስፋት ይነገራል፡፡ መሓሪና ይቅር ባይ ነው ሲባል እንዴት ነው? ማለት አንድ ሰው ችግር ገጥሞት ፈጣሪዬ ሆይ አድነኝ ብሎ ቢማጸን ወድያውኑ ፈጥኖ ለምን አያድነውም? ልክ አንድ አባት ልጁ አደጋ ውስጥ ሆኖ በኀዘን አባቴ ርዳኝ ብሎ ሲማጸነው በፊት የበደለውን በደል ረስቶ ፈጥኖ እንደሚያድነው ፈጣሪም ለምን ፈጥኖ አያድንም 30 ወይም 40 ዓመት ለምን ዝም ይለዋል? ብዙ ጊዜ ስለማይጠቅመን ነው ወይም ጊዜ ስላልደረሰ ነው ወይም ስለኃጢአታችን ነው የሚል ምክንያት ይቀርባል፡፡ እንዲህ ከሆነ የፈጣሪ ደግነቱ የታለ? ስለማይጠቅመን ነው ቢባል ሌላው የሚጠቀምበት ጤና ለእኔ ለምን አይጠቅመኝም ጊዜው ገና ነው ቢባል አርባ አመት ሙሉ መልስ ያላገኘ ጥያቄ መቼ ያገኛል?

መልስ፡- የእግዚአብሔርን መሓሪነት የሰው ልጅ መርምሮ እንዲህ ነው እንዲያ ነው ማለት አይችልም፡፡ እነዚህን ጥያቄወች ለመመለስ መጀመሪያ የመኖርን ምክንያት ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ለምን እንኖራለን? መኖር ካለመኖር ብልጫው ምንድን ነው? መሞታችን ካልቀረ የመኖራችን ጥቅም ምንድን ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዓለም ደስታ ብቻ ወይም ኀዘን ብቻ የለም፡፡ ደስታና ኀዘን፣ ጤናማነትና በሽተኛነት እየተፈራረቁ ይኖራሉ፡፡ ሰው በተለያየ ምክንያት ይታመማል፡፡ ከሕመሙ ለመዳን ወደ እግዚአብሔር ሊለምን ይችላል፡፡ እግዚአብሔርም ምላሽ

የሚሰጥበት ወቅት አለ። ምላሽ የማይሰጥበት ጊዜም አለ። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ በሽተኛ ነበር። በሽታውን እንዲያርቅለት እግዚአብሔርን ቢለምነውም እግዚአብሔር ግን በሽታውን አላራቀለትም (2ኛ ቆሮ.12፥7-10)። ቢታገሡት ሰማያዊ ዋጋን የሚያሰጥ በሽታ አለ። በኃጢአት ምክንያት የሚመጣ በሽታም አለ። በኃጢአት ምክንያት ለመጣው ንስሓ ገብቶ ሥጋውን ደሙን መቀበል ነው። ስለዚህ ከእኛ የማይርቅ በሽታ ካለ ብንታገሥና እግዚአብሔርን ከማመስገን ባንከለከል ሰማያዊ ዋጋን የሚያሰጠን ስለሆነ ለእኛ ጥቅም ሲባል የመጣ በመሆኑ እግዚአብሔር አያርቀውም። በተረፈ በግምት እናውራ ካላልን በስተቀር የእግዚአብሔርን ፍርዱንና ይቅር ባይነቱን እኛ የመመርመር አቅሙ የለንም። እግዚአብሔር በመልክ፣ በፆታ፣ በቁመትና በመሳሰሉት ልዩ ልዩ አድርጎ ፈጥሮናል። አንዱን አጭር አንዱን ረጂም፣ አንዱን ጤነኛ አንዱን በሽተኛ፣ አንዱን ቀይ አንዱን ጥቁር ለምን ያደርገዋል እያልን ባለችን ትንሽ አእምሮ ለመተቸት መጣር አይገባም። ምክንያቱን የሚያውቀው እርሱ ራሱ ብቻ ነው። የሕመማችንን ምክንያት ራሱን እግዚአብሔርን ሳንጠይቅና ሳይነግረን ደግነቱን ዝቅ ያደርገዋል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። ምናልባት ያ ሰው ጤነኛ ቢሆን የበለጠ ኃጢአተኛ የሚሆን ቢሆንስ? ለሰባ ሰማንያ ዓመት ጤነኛ ሆኖ ኃጢአተኛ ከሚሆን መቶ ዓመት በሽተኛ ሆኖ ገነት መግባት የተሻለ ነውና። እና እግዚአብሔርን በአካል አግኝተን ስለእያንዳንዱ ምክንያት ባልጠየቅንበት ሁኔታ የራሳችንን ድምዳሜ ወስደን ለመተቸት መሞከር አላዋቂነት ነው።

## ፴፱. በጳጕሜን ሳምንት ብዙዎች ሰዎች የጳጕሜን ውሃ ጠበል ነው እያሉ ወንዝ ወርደው ይታጠባሉና ይህ እንዴት ነው?

መልስ፦ ከነሐሴ መጨረሻ ጀምሮ ድፍርስ የነበረው ውሃ ይጠራል። ስለዚህ ሰው በምክንያት ወንዝ እየሔደ ይታጠባል። እንጂ የወንዙ ውሃ ጠበል ይሆናል ማለት አይደለም። በጳጕሜን ወንዝ እየሄዱ መጠመቅ ኢዮብ በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ቀን ተጠምቆ የመዳኑ ምሳሌ ነው። ስለዚህ ጠበል ካለ ከጠበል ቦታ እየሔዱ መጠመቅ ነው። ጠበል ከሌለ ደግሞ የኢዮብን መጠመቅ እያሰብን ወደማንኛውም ወንዝ እየወረድን መታጠብ ነው።

## ፵. ዲቁና ተቀብያለሁ እና ሳላገለግል ከሽፈብኝ። አሁን እኔ ቅኔና መጽሐፍ መማር እችላለሁ?

መልስ፦ ትችላለህ። ቅኔን፣ መጽሐፍን ሴቶችም ይማሩታል። ሴቶች ክህነት ኖሯቸው አይደለም። የመጽሐፍ ትምህርት ሃይማኖትን ለማወቅ፣ ሥነ ምግባር እንዲኖረን ለማድረግና ለመሳሰለው ትልቅ ጥቅም ስላለው ማንኛውም ክርስቲያን መማርና ማወቅ ያለበት ትምህርት ነው። ክህነትህ ከፈረሰ በክህነትህ አትቀጥልም። ከመማር ግን አትከለከልም።

**፶፮. እዚህ ምድር ላይ ያለ ሁሉም ሳይወድ እና ሳይፈቅድ ነው ወደዚህ ምድር የመጣው:: እና ያለ ፈቃዱ በመጣባት ምድር በሚኖረው ሕይወት በሠራው ሥራ ወደ ሲኦል መውረዱ ከእግዚአብሔር ፍትሐዊነት ጋር አይጋጭም?**

መልስ፦ አይጋጭም:: አዎ የሰው ልጅ ለመፈጠሩ ምክንያቱ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ነው:: ሰው ቀድሞ ስላልነበረ ሲፈጠር አስተያየት መስጠት አይችልም ነበር:: ነገር ግን ከተፈጠረ በኋላ ከሲኦልና ከገነት የፈለገውን መርጦ የመኖር ሥልጣን ተሰጥቶታል:: ስለዚህ ሲኦልም የሚገባ ገነትም የሚገባ በዋናነት በራሱ ምርጫ ነው:: ከእግዚአብሔር ፍትሓዊነት ጋር ምንም የሚያጋጨው ነገር የለም:: እንዲያውም ይህ የሚያሳውቀን የሰውን ምርጫ የሚያከብር እግዚአብሔር ምን ያህል ፍትሓዊ እንደሆነ ነው:: ሰው ያለፈቃዱ ወደዚህ ዓለም መጣ እንጂ ወደ ሲኦል ያለፈቃዱ አልገባም:: ጠያቂ ሆይ ቀላቀልከው:: ሰው ሲኦል የሚገባ በራሱ ምርጫ ነው:: የምርጫው መገለጫ ደግሞ ክፉ እየሠራ በመኖሩ ይታወቃል:: የሰው ልጅ ምን ቢሠራ ገነት፣ ምን ቢሠራ ደግሞ ሲኦል እንደሚገባ ተገልጿል:: ስለዚህ የሚመቸውን መርጦ መሥራት የራሱ የሰው ድርሻ ነው::

**፶፯. እንዴት የተለያየ ዓይነት ዜማ ብሂል ሊኖር ቻለ? የትኛው ነው ትክክል?**

መልስ፦ በየሀገሩ ሥርዓተ አምልኮን ለመፈጸም ልዩ ልዩ የዜማ ስልቶች አሉ:: የአርመን ቤተክርስቲያን፣ የግብጽ ቤተክርስቲያን፣ የሶርያ ቤተክርስቲያን፣ የሕንድ ቤተክርስቲያንና የሌሎችም የየራሳቸው ዜማ አላቸው:: ዜማው እግዚአብሔርን ማመስገኛ እስከሆነ ድረስ መለያየቱ የሚፈጥረው ችግር የለም:: በሀገራችንም የአጫብር ዜማ፣ የቤተልሔም ዜማ፣ የቆሜ ዜማ፣ ወንጨሬ፣ ተጕለቴ...ወዘተ እየተባለ ልዩ ልዩ ዜማዎች አሉ:: በሁሉም የሚመሰገን እግዚአብሔር ነው:: ስለዚህ ጉዳዩ በንጽሕና ማገልገሉ ላይ እንጂ የዜማው ልዩነት የሚፈጥረው ችግር የለም:: ሁሉም እግዚአብሔር እስከተመሰገነበት ድረስ ትክክል ነው::

**፶፰. በነገረ ሥጋዌ ርስት መቼ ይነገራል?**

መልስ፦ ርስት የሚለው ቃል ወረሰ ከሚለው ግሥ የወጣ ምዕላድ ነው:: በነገረ ሥጋዌ ምስጢሩ ሥጋ የቃልን ገንዘብ ቃልም የሥጋን ገንዘብ መውረሳቸውን የሚያመለክት ቃል ነው:: በጊዜ ተዋሕዶ የቃል ገንዘብ ለሥጋ ስለሆነ ርስት ከጊዜ ተዋሕዶ ጀምሮ ይነገራል::

**፶፱. በጾም ወቅት ይታረዳል ወይስ አይታረድም? ለምሳሌ አንድ ሰው ባለቤቱ በጾም ወቅት ብትወልድ ሥጋ ለመብላት ብትፈልግ አያርድም?**

መልስ፦ አንድ ሰው ሚስቱ በወሊድ ምክንያት ብዙ ደም ቢፈሳትና ሌሎችም ከባድ ሕመም ያለባቸው ሰዎች በፍትሐ ነገሥት አንቀጸ ጾም ላይም እንደተገለጸው ሥጋ ወተት ሊበሉ ይችላሉ። ስለዚህ ለሕሙማኑ መታረድ ይችላል። ጾመኛ ሰው ግን በጾም ወቅት ሥጋ ስለማይበላ አይታረድለትም።

፵፫. ደማዊት ነፍስ በትንሣኤ ትነሣለች? ደማዊት ነፍስስ አካል ናት? በደም ታድራለች የምትባለው ይች ናት ወይስ ለባዊቷ?

መልስ፦ አዎ ትነሣለች። የሰው ልጅ ደማዊት ነፍስ እየተባለች የምትገለጸውኮ ራሷ ደም ናት። ሰው ደግሞ ከነደሙ ከነሥጋው ስለሆነ የሚነሣ ደማዊት ነፍስ አዎ ትነሣለች። አካልም አላት። በደም ታድራለች የተባለች ነባቢት ነፍስ ናት። ነባቢት ነፍስ በደም ታድራለች። የሰው ልጅ ደሙ ፈስሶ ሲያልቅ የምታድርበት አጥታ ከሥጋ ተለይታ ወደ መካነ ነፍስ [ሲኦል ወይም ገነት] ትሄዳለች።

፵፬. አንድ ሕፃን በሰባት ወር ቢወለድ እና ሕፃኑን በሐኪም ትእዛዝ መሠረት ውሃ ውስጥ ማስገባት የማይፈቀድ እና ከተተከለበት oxygen መንቀል የማይቻል ቢሆን (አርባ ቀን ሞልቶታል) የጥምቀቱ ነገር እንዴት ይሁን?

መልስ፦ ይህ ጉዳይ አዲስ እንደመሆኑ አባቶች በብያኔ የሚወስኑት ነው። ቋሚ ሕግ ለዚህ አልተሠራለትም። ይሞታል ብለው የሚሰጉት ከሆነ ግን ከአርባ ቀን በፊትም ሄዶ ማስጠመቅ ይቻላል። ከሐኪሞች፣ ከሊቃውንት፣ ከጳጳሳት ጋር መክሮ የሚጠመቅበትን መንገድ ማመቻቸት ነው። ሐኪሞቹ ውሃ አይንካው ቢሉም ሕፃኑ የሚጠመቅበት ውሃ ግን በጸሎት ከክርስቶስ ጎን የፈሰሰ ማየ ገቦ በመሆኑ ምንም ጉዳት አያደርስበትም። ደግሞም ልጅነት ታላቅ ነገር ስለሆነ ከሕይወት ጋር የሚታይ እንጂ በትርፍ የሚታይ አይደለም።

፵፭. ካህን እና ዲያቆን ዐሥራት በኩራት ይከፍላሉ ወይስ አይከፍሉም?

መልስ፦ ይከፍላሉ። በብሉይ ኪዳንም ሌዋውያን ዐሥራት ያወጡ ነበር። ካህናት የሚኖሩት በዐሥራት በኩራት ገንዘብ ነው። ስለዚህ በዐሥራት በኩራት ካገኙት ገንዘብ ዐሥራትን ስለሚያወጡ የእነርሱ አሥራት የዐሥራት ዐሥራት ይባላል። "ለሌዋውያን እንዲህ ብለህ ንገራቸው ከእስራኤል ልጆች ለእናንተ ርስት አድርጌ የሰጠኋችሁን ዐሥራት በተቀበላችሁ ጊዜ ለእግዚአብሔር ለማንሣት ቊርባን የዐሥራት ዐሥራት ታቀርባላችሁ" እንዲል (ዘኍ.18፥26)።

፵፮. አብላካት እና አብሳላት ብሎ ስም ማውጣት ይቻላል ወይ?

መልስ፦ ይቻላል። ሁላችንንምኮ በተፈጥሮ ወደዚህ ምድር ያመጣን አብ ነው። ስለዚህ አንዲትን ሴት እግዚአብሔር እንደፈጠራትና ወደዚህ ዓለም እንዳመጣት ለመመስከር አብላካት አብሳላት ብትባል የሚያመጣው የምስጢር መፋለስ የለም።

፵፱. ጳጕሜን 3 ሰማይ ይከፈታል ይባላል። አከፋፈቱ እንዴት ነው? የሚከፈትበት ምክንያትስ ምንድን ነው?

መልስ፦ ሰማይ የሚከፈት የሚዘጋ ነገር አይደለም። ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስም የምስጢር መገለጥን፣ የምሕረት መውረድን የሰማይ መከፈት እያለ ይገልጸዋል። ጳጕሜን 3 ታላቁ መልአክ ቅዱስ ሩፋኤል መታሰቢያ በዓሉ ነው። በዚህ መታሰቢያ በዓሉ በምልጃው ብዙዎችን ይጠቅማልና ይህንን ለመግለጽ ሰማይ ይከፈታል እየተባለ ይነገራል እንጂ ይህ ወደላይ የምናየው ሰማይስ አይከፍትም አይዘጋም።

፶. አንድ ዲያቆን ቅዳሴ ከገባ በኋላ ነስር ቢነስረው አቋርጦ መውጣት ነው ያለበት ወይስ እስከ መጨረሻው ቆይቶ መቁርብ ነው ያለበት?

መልስ፦ አቋርጦ መውጣት ነው ያለበት። አንድ ሰው አካሉ ከደማ በቤተክርስቲያን እንዳይፈስ በልብስ አፍኖ ወዲያውኑ መውጣት አለበት። ቅዳሴውን በቀሩት ልዑካን መፈጸም ነው።